በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 1-31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ

## ግምገማ እንዲሁም

## ከአፕሪል 1-30/2024

## የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

አፕሪል 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........- 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........- 3 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ ........- 4 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........- 4 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........- 5 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........- 5 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........- 6 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ........- 6 -

ካርታ 7፡ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........- 7 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........- 8 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........- 8 -




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በማርች የመጀመሪያው አስር ቀናት በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በመካከለኛው፣ በምስራቅ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በሁለተኛዉ አስር ቀናት ደግሞ በምስራቅ፣ በመካከለኛው እንዲሁም በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ የዝናብ መጠን አግኝተዋል፡፡ በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ከህንድ ውቅያኖስ ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ እርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ይበልጥ በመጠናከሩ ምክንያት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎችን እንዲሁም በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግበዋል፡፡

በአጠቃላይ በማርች ወር በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በስርጭትም ሆነ በመጠን በርካታ የገሪቱን አከባቢዎች ያዳረሰ ሲሆን፤ በብዙ አከባቢዎች ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል፤ አዲስ አበባ ቦሌ 30.5፤ በቢሾፍቱ 30.2 እና 55.4፤ በድሬ ዳዋ 52.1፤ በጎሬ 39.8፤ በመተሃራ 68.6 እና 34.8፤ በአቦምሳ 96.0 እና 31.7፤ በአዳማ 54.1፤ በአማን 32..5፤ በአምቦ 31.7፣ በአምደ ወርቅ 34.0፤ በአዋሽ አርባ 34.0፣ በባቲ 32.0፤ በበደሌ 70.7 እና 42.7፤ በቦሬ 30.3፣36.2፤ በቡኢ 31.6፣33.5፣43.3፣51.0፣30.3 እና 36.2፤ በቡሬ 34.4፣39.3 እና 30.0፤ በቡርጂ 54.0፤ በጭፍራ 52.2፤ በጭራ 59.5፤ በዳሊፋጊ 35.4 እና 52.2፤ በድብረ ወርቅ 30.9፤ በዶሎመና 30.7 እና 80.0፤ በፍቼ 32.4፣ በገለምሶ 87.0፤ በጊኒር 30.0 በሀረር 41.7 እና 30.0፤ በሆሳና 42.0፤ በኮንሶ 33.5፤ በቁሉምሳ 30.2 እና 44.5፤ በሊሙገነት 44.7፤ በማሻ 30.6፤ በሜኤሶ 40.7፤ በማይጨው 31.5፤ በመተሃራ 68.6፤ በማጀቴ 44.1 እና 57.2፤ በማጂ 46.5፤ በማሻ 34.6፣30.0 እና 70.6፤ በአዳማ 54.1፤ በኑራኤራ 72.6፤ በሰንቃጣ 31.9፤ ተርጫ 48.9፤ በወራቤ 70.6 እና 30.1፤ በያቤሎ 34.5፤ በባቱ 71.5፤ በዉጫሌ 48.0፤ ቀሉቢ 46.1፤ ሂርና 48.1 እና 76.0፤ ግራዋ 40.0፤ በኩርፋ



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ጨሌ 30.5፤ በደንገጎ 22.6፣ በቀብሪ በያ 38.5፤ በጨለንቆ 41.7 በሚ.ሜ ይገኙበታል። በተጨማሪም ከነበረዉ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በቢሾፍቱ 55.4፣ በመተሃራ 68.6፣ በአቦምሳ 96፣ በጭራ 59.5፣ በዶሎመና 80፣ በማሻ 70.6፣ በሂርና 76 በሚ.ሜ አዲስ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል፡፡

ባለፉት በማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ ምስራቅ ጎጃም እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የማዕካላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ ዞን፣ አዲስ አበባ እና ሀረሪ ላይ 60-220 የሚደርስ ዝናብ ከ11-20 ቀናት ያህል ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ አኙዋክ እና ኑዌር ዞኖች፣ ሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሁሉም የትግራይ ክልል እና የአፋር ክልል ዞኖች ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ዶሎ፣ ኖጎብ አፍዴር እና ሊበን ዞኖች ከ10-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-9 ቀናት ያህል ነበራቸው (ካርታ 10 እና 11) ፡፡


ባለፉት በማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ አፍደዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የትግራይ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የሲዳማ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 2፣4፤5 እና 3፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ኑዌር ዞኖች፤አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሀረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 12 እና 13)።




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-44 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 2) ።

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው ወር የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አካባቢዎች እርጥበታማ ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ የረጅም ጊዜ ሰብሎችን አስቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማካሄድ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ (ካርታ 13)፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ወር በኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም የላይኛው እና የታችኛው ተከዜ እና አባይ ተፋሶች ላይ ከ እርጥበታማ እስከ ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ነበሩ፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድርን የውሃ ሀብትን እና የግድቦችን የውሃ አቅም ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል (ካርታ 14)፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ


በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል ወር የዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ የሚጠናከሩበት ወር ሲሆን፤ ከተቀሩት የበልግ ወራት አንጻር በጎላ መልኩ የዝናብ መጠንና ሥርጭቱ በብዙ ሥፍራዎች ላይ የሚስፋፉበት ወር ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለጎርፍ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በመጪው ወር ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚጠናከሩና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአጠቃላይ በሚቀጥለዉ ወር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፤ ቦረና፤ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል የምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የመካከለኛዉ እና የሰሜን ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የዋግህምራ ዞኖች፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚያዳርስ የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 5)። በተለይም በሰሜን ምስራቅ፤ ስምጥ ሸለቆ፤ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ የሚኖረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ የማስከትል አቅም ሊኖረው ስለሚችል ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡




ካርታ 7፡ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-30፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የአፕሪል ወር በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚዘሩ ሰብሎችም ሆነ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በተለያየ ምክንያቶች የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለጀመሩና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚጠበቀው እርጥበት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በቂ ግብዓቶችን ለመጠቀም ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሊኖር ከሚችለው በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል በተለይም ውሃ ገብና የአፈር ፀባያቸው በቀላሉ ውሃን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትን ሊያስከትልና በማሳዎች ላይ ውሃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ የበዛውን ውሃ በቀላሉ ለማጠንፈፍና ለማስወገድ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ከወዲሁ መተግበር ያስፈልጋል፡

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለዉ ወር በኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል እና አይሻ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የላይኛው እና የታችኛው ተከዜ እና አባይ ተፋሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድርን የውሃ ሀብትን እና የግድቦችን የውሃ አቅም ከማሻሻል አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በተወሰኑ ተፋሰሶች ላይ በተደጋጋሚ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ማግኘታቸውን ተከትሎ የወንዞች መሙላት እንዳይከሰት የስጋት አካባቢዎችን በመለየት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et